**የተከበረው ያገራችን ሕዝብ**

**የተከበረው የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ**

**የተከበራችሁ የአንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ አባላት**

**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ**

**አንድነት መድረክ አባላት**

**የተከበራችሁ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ወኪሎች**

**የተከበራችሁ እንግዶች**

ዛሬ ሕዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፊታችሁ የቆምኩት፣በታላቅ ድፍረት፣በታላቅ ኩራትና በታላቅ ደስታ፣እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሕገ-መንግሥቱ የተከበሩልኝን መብቶች በመጠቀም ከዛሬ ጀምሮ የአንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ (አንድነት) አባል ለመሆን መወሰኔን በይፋ ለማስታወቅ ነው:: አንድነት በአባልነት ከተቀበለኝ ባለኝ አቅም ሁሉ፣በሕገ-መንግሥቱ፣ባገሪቱ ሕጐችና በፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የአባልነት መብቴን እየተጠቀምኩ የአባልነት ግዴታዬን ለመወጣት የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆኔን አረጋግጣለሁ::

**ክቡራትና**

**ክቡራን!**

ባለፉት ጥቂት ዓመታታ ሁለት ሁኔታዎችን ለመታዘብ ችያለሁ:: የህዝባችን ልዩ ልዩ ክፍሎችና ያገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ለኔ ያላቸውን ፍቅርና አድናቆት መግለፃቸው አንዱ ሁኔታ ነው:: ይህ ፍቅርና አድናቆት ለኔ ትልቅ ገንዘብና ሃብት ነው:: ስለሆነም አድናቆታችሁንና ፍቅራችሁን ስለገለፃችሁልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው:: ደስታዬንና ምስጋናዬን የምገልጽባቸው ቃላቶችም ያጥሩኛል::

ሁለተኛው ሁኔታ በዚህ በሕዝባችን አድናቆትና ፍቅር በኩል አንድ መልእክት እየተላለፈ መሆኑን መረዳቴ ነው:: ይኸውም ያገራችንን ብሔር ብሔረሰቦችና ዜጐችን ሳላበላልጥ ሁሉንም እኩል እንዳገለግል ፍላጐታቸው መሆኑን ነው:: ስለሆነም ይህ የዛሬ ውሳኔዬ ይህን የሕዝቡን መልእክት መስማቴንና መቀበሌን እንደሚገልጽ እምነቴ ነው::

እንደሚታወቀው የእድሜዬን አብዛኛውን ክፍል ያሳለፍኩት በኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ውስጥ ነው:: ከዚህም የተነሳ ነጋሶ ስለ ሌሎች ብሔሮችና ስለ አገሪቱ ባጠቃላይ አያስብም ይላሉ:: እርግጥ ብሔርተኛ ድርጅቶች፣አጠቃላይ አገራዊ ይሁን ብሔር ብሔረሰባዊ፣ነገሮችን አስፍተው ያለማየቱ ችግር አለባቸው:: ብሔርተኞች የእንቁላ ሽፋንዋን ገና ሰብራ እንዳልወጣች ጫጩት ናቸው:: ጫጩትዋ በእንቁላል ሽፋንዋ ተሸፍና አስካለች ከዚያ ውጭ ያለውን ለማየት አትችልም:: እኔ ግን ያንን እንቁላል ሰብሬ ሌላ አቅጣጫ ማየት የጀመርኩት በ1983 ዓ.ም ወደ አገር ለመመለስ በወሰንኩበት ወቅት ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለዩነቶችንም የምታከብርና የምታስተናግድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትፈጠርና እንድትገነባ እታገልኩ ነው:: ሆኖም ግን አንዴ ጄኔራል ታደሰ ብሩ የገለጹት ሆኔታ ሲፈጠር ካየሁ አንጀቴ መቃጠሉና ነገሮች እንዲስተካከሉ መጮሄ አይቀርም:: ጄኔራል ታደሰ በጥቅምት 21 ቀን 1958 ማታ የነበረውን ሁኔታ ሲገልጹ «እዩ የአዲስ አበባ አካባቢ የሸዋ ገበሬ ከብቱ ለምትበላው ሳር ቀረጥ ይከፍላል፣ላም የምትጥለውን ቆሻሻ አሰባስቦ አድርቆ ኩበቱን ወደ ገበያ ሲወስድ በአህያው ጭኖ ወደ ገበያ በሚወስደው ኩበት ላይም ቀረጥ ይከፍላል:: ላሞቹም ተቆጥረው ቀረጥ ይከፍልበታል:: መሬቱ ተወስዶበት እርሱ ለባላባቱ ግብር ይከፍላል:: ይህን ሁሉ እያደረገ ለሸዋው ገበሬ ት/ቤቶችንና የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አልተገነቡለትም፣ይህ ሁኔታ መለወጥ አለበት» ይሉ ነበር:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ብቻ አይፈጸምም ነበር፣በሌሎችም ላይ ይፈጸም ነበር:: ለውጡም ለኦሮሞ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም እንዲሆን ምኞቴ ነው:: በኦሮሞ ድርጅቶች በመታቀፍ ታገልኩ:: ለውጥ አልመጣም:: የኦሮሞ ድርጅት አባል በሆነበት በኢህአዴግ ታቅፌ ትግል ጀመርኩ:: ለኦሮሞም ሆነ ለሌላው ለውጥ አልመጣም:: ከዚህ አኳያ ነው እስቲ ከተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ተወላጆች በተቋቋመ ሕብረ ብሔራዊ ድርጅት ገብቼ በአመለካከት በአደረጃጀትና በአሠራር ትግሌን ልቀጥል ብዬ ማሰብ የጀመርከት:: ከዚህም አኳያ ነው የአንድነት አባል ለመሆን የወሰንኩት::

**ክቡራትና**

**ክቡራን**

አንድነት ለግለሰቦች መብት መከበርና ለኢትዮያ አንድነትና ሉዓላዊነት ቅድሚያ ይሰጣል እንጂ ጠባብ የኢትዮጵያ ብሔርተኛ ድርጅት አይደለም:: ይህን በግልጽ ለማየት የቻልኩት የመድረክ መለስተኛ ፕሮግራም ለመንደፍ ረጅምና አድካሚ ስብሰባዎች ስናካሂድ በነበርንበት ወቅት ነው:: ጠባብ ብሔርተኛ ያለመሆኑንም በራሱ ፕሮግራምም ያሳያል:: በነገራችን ላይ እንደ አንድነት እንደ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄና እንደ ኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ሕብረ ብሔራዊ ድርጅቶች በጋራ መሥራት የማይናቅ ኃይል መሆኑን ማሳየት ብቻ ሳይሆን ሌላም ውጤት አስገኝቷል:: መድረክ ለረጅም ጊዜ ሳያቋርጥ የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲሰፋና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ አመቺ ሁኔታ ይፈጠር ብሎ ሲጮህ ነበር:: በዚህ የመድረኩ እንቅስቃሴ ምክንያት ነው ኢህአዴግ ለድርድር ጥሪ እንዲያደርግ የተገደደው::

ያም ሆነ ይህ አንድነት ከምስረታው ጀምሮ ሲያደርግ የቆየው እንቅስቃሴና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ እንዲመሰረት ያበረከተው አስተዋጽኦ አስደስቶኛል፡፡ ስለሆነም አንድነትን መቀላቀሉ ይጠቅማል የሚል እምነት ካደረብኝ ውሎ አድሮአል፡፡ በሌላ በኩልም መድረክን ለማጠናከር ፍላጐት አለኝ፡፡ የመድረክ መጠናከር አንድነትን ያጠናክራል፡፡ በተዘዋዋሪም የአንድነት መጠናከር መድረክን ያጠናክራል፡፡ መድረክን የማጠናከር ፍላጐቴ እውን ሊሆን የሚችለው የፖለቲካ ድርጅቶች ሕግን በመከተል በአንድነት በኩል የመድረክ አባል ሲሆን ነው፡፡ የመድረክ መጠናከር ደግሞ አንድነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም የመድረክ አባል ድርጅቶች መጠናከር ነውና፡፡

የአንድነት አባል ለመሆን የወሰንኩበት ሌላም ምክንያት አለ፡፡ አንድነት ተመስርቶ ብዙም ሳይቆይ የድርጅቱ ሊ/መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሣ ከታሠረች ይኸው አንድ ዓመት ሊሆን ነው፡፡ አንድነት በዚህ ችግር ውስጥ እያለ የተለያዩ መሠረታዊ ያልሆኑ ምክንያቶችን በመደስኮርና በማግዘፍ ከድርጅቱ መራቅና ድርጅቱን ለመጉዳት መንቀሳቀስ ወ/ሪት ብርቱካንንም አይጠቅምም፡፡ ይልቁንም ድርጅቱን በማጠናከር ብርቱካንን ለማስፈታት የሚካሄደው ሕዝባዊ ትግልና እንቅስቃሴ እንዲያድግና እንዲጠናከር አስተዋጽኦ ማበርከት የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ወ/ት ብርቱካን የማስፈታት እንቅስቃሴ ተሳታፊም ለመሆን ነው አንድነትን የምቀላቀለው፡፡ ለኔ ብርቱካን ባገራችን የመጀመሪያዋ ወጣት ሴት መሪ ብቻ አይደለችም፡፡ የብርቱካን መታሰር ባገራችን የተንሰራፋው የሰብአዊ መብትና ነፃነት ጥሰት ግልጽ ማሳያ ምልክት ነች፡፡ ብርቱካን የፖለቲካ እሥረኛ ነች እንጂ ወንጀለኛ አይደለችም፡፡ የፖለቲካ እሥረኞች ባገራችን እንዲኖሩ መፍቀድ የለብንም፡፡ ብርቱካን ሚደቅሣና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ባስቸኳይ እንዲፈቱ ባንድ ድምጽ መጠየቅ አለብን፡፡ ብርቱካን ሚደቅሣ የሰላማዊ ትልግ አርበኛ፣የሕገ-መንግሥታዊ ስርዓትና የሕግ በላይነት ጠበቃ ነች፡፡ ብርቱካን ሚደቅሣ ከነጋንዲና ከነ ማርቲን ሉተር ደረጃ የምትታይ የሰላማዊ ትግል መሪ ነች፡፡ ለእውነትና ለፍቅር ፀንታ በመቆምና ትክክለኛ አቋም ነው ብላ ለምታምንበት ዓላማ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆኗ እውነትም የኢያሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ያደርጋታል፡፡ እንዲህ ዓይነት መሪ ባስቸኳይ ትፈታ ዘንድ ጥሪያችንን ከፍ አድረገን እናሰማለን፡፡ ላገራችን ያላትን ራዕይ እውን ለማድረግ የመንቀሳቀስ በተለይ ለሴቶችና ወጣቶች ጥሩ ተምሳሌትና መሪ እንድትሆን ማብቃት አለብን ብዬ አምናለሁ፡፡

**ክቡራትና**

**ክቡራን**

የአንድነት አባል ለመሆን የወሰንኩበትን ምክንያቶች በተመለከተ ይህን ያህል ካልኩ በኋላ ስለ አንድነት አንዳንድ እምነቶችና አቋሞች ትንሽ ልበል፡፡ አንድነት በትክክል የተረዳው አንድ

ሃቅ አለ። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የግለሰብ ቦታና ሚና ቁልፍ ነው። ጤናማ ያልሆኑ ግለሰቦች ባንድ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ ያማህበረሰብ ጤናማ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም የግለሰብ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ሙሉ በሙሉ መከበር አለባቸው። የቡድን ወይም የወል መብትን በማስከበር የግለሰብ መብቶችና ነፃነቶች መጨፍለቅ ወይም መታፈን የሌባቸውም።

በአንፃሩ ደግሞ የግለሰብን ህልውና ለማስጠበቅ ግለሰቦች በተናጠል ብቻ ሳይሆን በጋራ ይንቀሳቀሳቀሳሉ። ግለሰቦች መብታቸው እየተጠበቀ ለጋራ ህልውና ዳግም የሚወጡት ግዴታዎች አሉ። ስለሆነም ለግለሰብና ለቡድን መብቶች መከበር መታገል ትክክል ነው። እስካሁን ባለው የአገራችን ባሕላዊና ፖለቲካዊ ሂደት ለግለሰብ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ተገቢ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር። ይህ መስተካከል ይኖርበታል። የግለሰብ መብትን ጉዳይ በመለጠጥ የቡድን መብቶች መከበርን ዋጋ ልናሰጠው አይገባም። ለሁለቱም የሚሰጡ ትኩረቶች ሚዛናቸወን መጠበቅ አለባቸው። ከዚህ አኳያ አንድነት ለሁለቱም መብቶች መከበር ሚዛናዊ አቋም መያዙ ትክክለኛ ነው።

ይህን አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ መንቀሳቀስ ለአገራዊ ስሜት መጠናከር ወሳኝ ነው። መብቴ የተከበረባት አገር አለኝ የሚል አመለካከት ይሰርፃል። ይህም ብቻ አይደለም። ዜጐች የነፃነት መንፈስ እየተነፈሱ ከኖሩ ሰላምና መረጋጋት ይጠናከራል። በዚህ ሁኔታ ነው ቀጣይ ልማትና እድገት ተካሂዶ የዜጐች ብልጽግና የሚመጣው።

የአገራችንን ህልውና እየተፈታተኑ ላሉት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በተመለከተ ሁላችሁም ስለምታውቁ እነሱን በመዘርዘር ጊዜአችሁን ለመወሰድ አልፈልግም። በተጨማሪም በአገራችንም ሆነ በአካባቢያችን አስተማማኝ መረጋጋትና ሰላም የለም። የፀጥታና የደህንነት ችግር አለ። የሽብርተኝነት አደጋም እያንዣበበብን ነው። እነዚህን ችግሮች በጋራ እንጂ በተናጠል በግላችን የምንሮጥ ከሆነ ችግሮቹን ወደ ማባባስ ብቻ ሳይሆን ወደ ማያቃርጡ ግጭቶችና እርስ በርስ መጠፋፋት አቅጣጫ እንገሰግሳለን። ይህን አደጋ ያለመረዳትና እንደቀላል ማየቱ ሃላፊነት የጐደለው አካሄድ ነው። ይህን አደጋ የሚያቀጣጥሉ ርዕዮተ ዓለሞች በተለይም ብሔርተኝነቶች እንደፈለጉ እንዲጋልቡ መፍቀድ የለብንም። በኔ እምነት ያገራችንን ችግሮች ለመፍታትና አደጋዎችን ለመጋፈጥ የእያንዳንዱ ዜጋና የሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ቡድኖች እንዲሁም የሁሉም ብሔርብሔረሰቦች ሃላፊነትና ግዴታ ነው። ከዚህ አኳያ የአገራችን ብሔር/ብሔረሰቦች አስተዋጽኦ አስፈላጊ ቢሆንም ከትላልቆቹ ብሔሮች ብዙ ይጠበቃል። ለዚህም ነው አንድነት ለዴሞክራስና ፍትህ ፓርቲ ስለአንድነት የሚጮኸውና በሕብረ ብሔራዊ አቅጣጫ ተሰባስቦ መንቀሳቀስ ጠቃሚ ነው የሚለው።

ሌላው ያገራችን ችግር ቅራኔዎችን ለመፍታት የምንጠቀምባቸው ስልቶች ናቸው። የተለያዩ ቅራኔዎች የተለያዩ የቅራኔ አፈታት ስልቶች አሏቸው። የፖለቲካ ቅራኔዎችና ጥያቄዎች በፖለቲካዊ ስልት ካልተፈቱ ወደ ውስብስብና ቀጣይ ቅራኔዎች ይሄዳሉ። ቅራኔዎችን በኃይል መፍታት መሞከር ጉጂ ነው። ቅራኔዎቹም በኃይል ይፈታሉ ብሎ ማመንም ሆነ መተግበሩ በጣም ስህተት ነው። በኃይል መፍታት አይቻልምም።ይህን በመገንዘብ ይመስለኛል

አንድነት በፕሮግራሙ ዐቢይ የፖለቲካ ጥያቄዎችን የፖለቲካዊ መልስ እንዲያገኙ ይህም በፖለቲካዊ ምላሽ በኃይል ሳይሆን በሠላማዊ ዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ መንገድ ሆኖ ቢቻል በውይይትና በድርድር ይሆናል የሚለው ይህ ካልተቻለ ግን ጥያቄው ወደ ሕዝብ ተመርቶ ሕዝቡ ውሳኔውን እንዲሰጥበት ይደረጋል «ብሎ» ያስቀመጠው ትክክለኛ አቋም ነው:: የአቋሙ ትክክለኛነት በቅራኔ አፈታት ስልቱ ብቻ አይደለም:: አቋሙ ሌላም ይዘት አለው:: አንድነት የሕዝብን ሉአላዊ የስልጣን ባለቤትነትና ወሳኝነትን በዚህ አቋሙ አስመስክሮአል:: ይህ አቋም የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች በሰላማዊና በሕገ-መንግሥታዊ መንገድ በመንቀሳቀስ ለዴሞክራሲ ግንባታና ለአገር አንድነት መጠናከር ወሳኝ ሚና የሚኖራቸው:: ለዚህ አቋም በተግባር መታየትም ቁርጠኝነቱን ያሳያል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ::

## ክቡራትና ክቡራን

ሃሳቤን ከማጠቃለሌ በፊት በወቅታዊ ሁኔታ ላይ ጥቂት ሃሳቦችን ጣል እንዳደርግ ይፈቀድልኝ:: ወቅቱ ለግንቦት 2002 ምርጫ የምንዘጋጅበት ሁኔታ ነው:: አሁን ያለንበት ወቅት ከ15 ዓመታት በፊት የነበረውን አንድ ክስተት ያስታውሰኛል:: ቀኑ ሕዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም ነበር:: በዚያን ዕለት የሕገ-መንግሥት ጉባኤ ሥራውን አጠናቅቆ ጉባኤያተኞች ሕገ-መንግሥቱን ማጽደቃቸውን በፊርማቸው አረጋገጡ:: በእለቱ በተከናወነው የመዝጊያ ስነ-ሥርዓት ላይም ንግግር አድርጌ ነበር:: በዚያ ንግግሬ ውስጥ የሚቀጥለው ይነበባል::

«ከረቂቅ ዝግጅቱ ጀምሮ እስከ ጉባኤው አባላት ምርጫ ድረስ የነበረው የሕገ-መንግሥቱ ሂደት ዴሞክራሲያዊ ነው መላ የአገሪቱ ሕዝቦች በነፃና በስፋት የተሳተፉበት ሁሉም አስተሳሰቦች በነፃ እንዲንራሸሩ ሰፊ ዕድል ያገኙበት ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በነፃ እንዲንቀሳቀሱና እንዲወዳደሩ የተመቻቹ ሁኔታዎች የነበሩበት ሂደት መሆኑን ጉባኤው አረጋግጧል»

የምታስታውሱ ከሆነ በዚያን ጊዜ እነ ኢህአፓና እነመኢሶን በአገር ቤት እንዳይንቀሳቀሱ ተደርጐ ነበር:: ኢሠፓ ከነጭራሹ እንዲታገድና እንዲፈርስ ተደርጓል:: እነ ኦነግና እነ ኦብነግ እንዲሁም ሌሎች ፓርቲዎች ከሂደቱ ተባረው ነበር:: ታድያ የዚያኔ ንግግሬ ተጨባጭ ሁኔታውን ይገልጽ ነበር? ውሸት አልነበረም? ስለዚህ ጉዳይ በተለያዩ ጊዜያት አንስቼ ሂደቱ ትክክል እንዳልነበረ ገልጬ ነበር:: ሆኖም ግን ይህ ንግግር እስካሁን ከሚያሳዝኑኝና በጣም ከማፍርባቸው ድርጊቶቼ አንዱና ዋነኛው ነው:: በጉዳዩ እስካሁንም አፍርበታለሁ፣ፀፀቱም አላበቃም:: በታሪክም ተመዝግቦ ይኖራል:: ይህን ልለውጠው አልችልም:: ያም ሆነ ይህ አንድ ለማድረግ የምችለው ነገር አለ:: የአገሬን ሕዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች በዚህ ስህተቴ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ አበክሮ መለመን ነው:: የዚያን ጊዜ ንግግሬ ትልቅ ስህተት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ራስን መዋሸትና ማታለል ነበር:: ዛሬም ቢሆን የፖለቲካ ምህዳሩ በጠበበትና ለአንዳንዶቹም ከነጭራሹ በተዘጋበት ሁኔታ ስለዴሞክራሲያዊና ተአማኒት ስላለው ምርጫ እናካሂዳለን ተብሎ ይነገረናል:: በ1987

አብረን ሆነንና በደስታ ተቃቅፈን ፎቶ የተነሳነው የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ መለስ ዜናዊ ያኔ የፈፀምነው ስህተት እንዳይደገም ለማድረግ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እየሠሩ ናቸው ብዬ ለማመን እቸገራለሁ:: እንደ አንድ የቀድሞ የሥራ ባልደረባ የዚያን ጊዜ ስህተታችንን እንዳይደግሙ ምክሬን ላስተላልፍላቸው እወዳለሁ:: ጆሮአቸወን ከሰጡኝ:: የማስተላልፍላቸው መልዕክቶች የሚከተሉት ናቸው:-

1. የፖለቲካ ምህዳሩ ለሁሉም ሠላማዊና ህጋዊ ፓርቲዎች እኩልና ፈትሃዊ መሆኑን ለማረጋገጥ እርስዎ የሚመሩት የፖለቲካ ድርጅት በሕገ-ወጥ በመንግሥት (በሕዝብ) ንብረት ገንዘብና የሰው ኃይል ሲጠቀም እንደነበር በይፋ ይመኑ:: ይህም ከፍተኛ ሙስና መሆኑን ይመኑ:: ይህ ሁኔታ ባፋጣኝ እንዲስተካከል መመሪያ ያስተላልፉ:: ባለፈው ቅዳሜ የምርጫ ስነ-ምግባር ደንብ መፈራረሙና እንደሚከበርም ለገለጹላቸው ወጣቶች ይህንንም ጉዳይ እንዲከታተሉና የፈለጉትን ድርጅት የመምረጥ መብት እንዳላቸው መልእክት ያስተላልፉላቸው::
2. ብርቱካን ሚደቅሣና ሌሎች የፖለቲካ እሥረኞች የምራጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት እንዲፈቱ ሁኔታን ያመቻቹ::
3. ሁሉም ሕጋዊና ሠላማዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ከዚህ ሳምንት ጀምሮ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በመንቀሳቀስ የድርጅት ሥራዎቻቸውን እንዲያከናውኑ ለዚህም ቢሮቻቸውን ባስቸኳይ ለመክፈት እንዲችሉ ምንም ዓይነት እክል እንዳይገጥማቸው መመሪያዎችን በሚድያ ያስተላልፉ:: የመንግሥት ሚዲያዎችም ያለአድልዎ ሁሉንም ፓርቲዎች እንዲያገለግሉ ትዕዛዝ ያስተላልፉላቸው::
4. በሕገ-መንግሥቱ የተደነገጉትን የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶችን የሚጻረሩ ሕጎች እንዲቀሩ ወይም እንዲሻሻሉ ሁኔታዎችን ያመቻቹ::
5. የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ በህቡዕና በውጭ አገር የሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ኃይሎች ወደ ሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲመጡ ማድረግ መንግሥትም ከነሱ ጋር ውይይትና ድርድር እንዲጀምር ሁኔታዎችን ያመቻቹ::

ይህ ከሆነ ነው የ1987 ስህተት መስተካከሉን የምናየውና የምርጫ 2002 ተአማኒነቱ የሚረጋገጠው:: በጠበበና በተዛጋ የፖለቲካ ምህዳር ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ምርጫ ይካሄዳል ማለት ራስን ማታለል ነው::

**ክቡራትና ክቡራን**

በዚያው የህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም ንግግሬ ሌላ የተናገርኩት ቁም ነገርም አለ:: እንዲህ ይነበባል:-

«ሕገ መንግሥቱ የመለሳቸው አበይት ጉዳዮች በተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ቀጣዩ ትኩረታችን ይሆናል:: በሕገ መንግሥት የምትመራ አዲሲቱን ኢትዮጵያ የሚገነባ የሕዝባዊ

መንግሥት ምስረታ ተግባር ይጠብቀናል። ይህ ደግሞ የመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። ሕገ መንግሥቱን የሚጠብቅ ሕገ-መንግሥቱን የሚተገብር ፖለቲካዊ ስልጣን ካልመሠረትን በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጡ የሕዝቡ ፍላጐቶች መከላሸታቸው እንደማይቀር የሚታበል አይደለም። ሕዝባዊ መንግሥት የመመስረቱ ተግባር ከሁሉም በላይ የሕዝቡ ሃላፊነት በመሆኑም ህዝቡ በብቃት እንዲከታተል በቅርቡ በሚካሄደው ምርጫ ተካትቶ እንዲመዘገብና ወኪሎቹን እንዲመርጥ ጉባኤው ያሳስባል።»

ይህ ንግግር በዛሬው እለትም የሚደገምና ለወቅቱ ሁኔታ የሚሆን ተገቢ መልእክት ነው ብዬ አምናለሁ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጀግንነቱ የታወቀ ነው። ስለሆነም ዘንድሮም ጀግንነቱን እንደገና ያስመሰራክል የሚል ተስፋና እምነት አለኝ። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖተኛ መሆን የታወቀ ነው። መልካም ጊዜ እንዲመጣና ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ዘወትር ይፀልያል።

የእግዚአብሔር፣የአላህም፣የያህዌም፣ሆነ የዋቃ መንግሥት መገለጫዎች ፍቅር፣ፍትህ፣እውነት እኩልነት፣የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች በሙሉ መከበር፣ሠላምና ብልጽግና ናቸው። ሆኖም ግን እነዚህ የአምላክ መንግሥት መገለጫዎች ርቀውናል። ስለሆነም ይህ ሁኔታ እንዲቀየር አሁንም በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም አባታችን ሆይ . . . እያልን ሃቀኛ ሃይማኖተኞች መሆናችንን እናስመስክር። በሁሉም መስክ ለውጥ ያስፈልገናልና።

ሕዝባችን ችግሮቻችንን ለመፍታት ብቃት እንዳለው በፍጹም አልጠራጠርም!!!

በጋራና በአንድነት ከተንቀሳቀስን የማንፈታው ችግር አይኖርም!!!

አመሰግናለሁ

ነጋሶ ጊዳዳ

<u>አዲስ አበባ</u>

**17/03/02**